የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 55
ADDIS ABABA - 30th June, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፭/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ስለጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣ (ማሻሻያ)
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፯፻፺፰

## CONTENTS

Proclamation No. 125/1998
Customs Authority (Amendment)
Proclamation ........................................... Page 798

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፭/፲፱፻፺

## የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ዘመናዊ አሠራር እንዲኖረው ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ ለማበረታታት፣ ለንግዱ ኅብረተሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ይበልጥ ቀልጣፋ ለማድረግ፣ የአገሪቱን የንግድ፣ የፊስካልና ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች በብቃት ለማስፈጸም የሚረዳ፣ የወጪ ንግድ መረጃን በፍጥነት ለማጠናከርና ለመጠቀም የሚያስችል የጉምሩክ አውቶሜሽንና የመረጃ ሥርዓት (አሲኩዳ) ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የጉምሩክ አውቶሜሽን የመረጃ ሥርዓት ሥራ ላይ ሲውል ሥራውን ሊያፋጥኑ የሚችሉ፣ ለንግዱ ኅብረተሰብ ፈጣን አገልግሎት ሊያስጡ የሚችሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን አሠራሮች ይዞ መጓዝ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ከነዚህም ጋር የሚቃረኑትን መተው በማስፈለጉ፣

ለዚሁም ስለጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 125/1998
## A PROCLAMATION TO AMEND THE RE–ESTABLISHMENT AND MODERNIZATION OF THE CUSTOMS AUTHORITY PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to introduce the Automated System for Customs Data and Management (ASYCUDA), with a view to accelerating the effort to modernize the Customs Authority, improving the efficiency of its services to the business community, effectively implementing the country's trade or fiscal and other related policies as well as to instantly compiling and utilizing foreign trade statistics;

WHEREAS, introduction of the customs automated system requires not only compliance with practices that are conducive, help provide efficient services and are internationally recognized but also removal of those that are to the contrary;

WHEREAS, to this end, an amendment to the proclamation relating to the Customs Authority is called for;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ስለጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፭/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

ስለጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፶፩ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፩ ተተክቷል ፤

"፶፩. <u>የገንዘብ ምንዛሪ</u>

ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡትም ሆነ ወደ ውጪ አገር ለሚላኩ ዕቃዎች ለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላው፡ ዲክሌር ስለተደረገው ዕቃ የቀረበው ዲክላሬሽን በጉምሩክ ባለሥልጣን ተቀባይነት ባገኘበት ዕለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ሲባል የተሰጠውን የምንዛሪ ልክ በመጠቀም ይሆናል።"

<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

1. ***Short Title***

This Proclamation may be cited as the "Customs Authority (Amendment) Prclamation No. 125/1998."

2. ***Amendment***

Article 51 of the Customs Authority Proclamation No. 60/1997 is hereby repealed and replaced by the following new Article 51:

"51. *Exchange Rate*

For customs taxes and duty calculation purposes, on value of goods imported into the country or exported out of the country, the exchange rate shall be the official rate declared by the National Bank of Ethiopia on the day of accepting customs declaration by the Customs Authority."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 30th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE